የቅጣት አወሳሰን በኢትዮጵያ የወንጀል የፍትህ ስርአት

በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ የቅጣት አወሳሰን መሰረታዊ መርሆዎች

- የወንጀል ቅጣት ሲወሰን ፍ/ቤቶች የተለያዩ ነገሮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።
- የህጉን ዓላማና መንፈስ መከተል፤ በወንጀል ህግ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶ ከሚቀረፁ ድንጋጌዎች መካከል ዓላማና ግቦች ይገኙበታል።
- በአንድ ህግ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለፁ ዓላማና ግቦች ህጉ የቆመበትን ምክንያትና የሚታሰበውን ውጤት ጠቅለል አድርገው የሚያመለክቱ ናቸው።

የቀጠለ

- ወንጀል ማህበራዊ ክስተት እንደመሆኑ መጠን በማናቸዉም ጊዜ ህጉ ያስቀመጠዉን ማስጠንቀቂያ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ሊፈፀም ይችላል።
- ይህ በሆነ ጊዜ ቅጣት የማይቀር ሆኖ ይመጣል።
- ስለዚህ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ውስጥ ቅጣት ግብ ሣይሆን የወንጀል መከላከሉን ግብ ለማሣካት የተቀመጠ አንዱ ስልት ነው።

የቀጠለ

- የወንጀል ህግ ሕብረተሰብን ከጉዳት ለመጠበቅ ሲባል የሚወጣ ነው፤
- የሕብረተሰብን ሰላምና ደህንነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በየጊዜው የሚኖሩ ለውጦችን ለማስቀጠል የሚያግዝ ቁልፍ መሣሪያ ነው።
- አንድ ህግ ሲወጣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈታው ችግር ይኖራል። ህጉ የሚፈፀመዉም የተቀመጠውን ዓላማ ለማሣካት ነው።
- ነገር ግን አፈፃፀሙ ከህጉ ዓላማ በተቃራኒ የሚሄድ ከሆነ አለ የተባለውን ችግር መፍታት ቀርቶ ህጉ ራሱ ሌላ ችግር ይሆናል።

የቀጠለ

- ቅጣቶችና የጥንቃቄ ርምጃዎች የሚወሰዱት ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማሳካት ሲሆን አፈፃፀማቸውም የህጉን መንፈስ መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባል።
- በአጠቃላይ የህጉን ዓላማና መንፈስ የተከተለ ቅጣት መወሰን አንዱ የቅጣት አወሳሰን መርህ ሆኖ እናገኘዋለን።

የአጥፊውን የግል ሁኔታ፣ የወንጀሉን ከባድነትና አፈፃፀም መሠረት ያደረገ ቅጣት

- ይህንን መርህ በተመለከተ የተለያዩ አስተሣሰቦች ይራመዳሉ።
- በተለይ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀሉን ከባድነት በማዬት የወንጀል አድራጊውን ዓላማና ግላዊ ሁኔታዎችን በማመዛዘን፣ የወንጀሉን ከባድነት ለብቻ በመመዘን ወይስ የተጠቀሱትን በሙሉ በአንድነት በማገናዘብ የሚል ጥያቄ ያስነሳል።
- በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ቁጥር 88 (2) እንደተደነገገው ቅጣት የሚወሰነው የወንጀል አድራጊውን የአደገኝነት መጠንና ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የአሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በመመዘን ነው።

ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በመመርመር መወሰን

- የሀገራችንን የቅጣት አመዳደብ ስርዓት ስንመለከት ህግ አውጭው ለአንድ የወንጀል ድርጊት ያስቀመጠው መነሻ እና ጣሪያ አለ።
- የህጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቶች በህጉ ቁጥር 88 (3) ላይ እንደተመለከተው እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ተገቢ የሆነውን ቅጣት መወሰን አለባቸዉ።
- ይሁንና እንደነገሩ ሁኔታ የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክኒያቶች ካሉ በህጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌ ከተመለከተው መነሻ ቅጣት ዝቅ ወይም ጣራው ከፍ አድርጎ ለመወሰን የሚቻል ይሆናል።

የአወሳሰንን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ማረጋገጥ

የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አዉጥተዉ በተገበሩ አገሮች እንዲሁም ስለቅጣት አወሳሰን በተጻፉ የምርምርና የጥናት ጽሁፎች ከቅጣት አወሳሰን ጋር በተያያዘ የቅጣት አወሳሰን ሊገዛባቸው የሚገቡ መርሆዎችን ያስቀምጣሉ። እነዚህም

- ተመዛዛኝነት/proportionality/፦
- ይህ መርህ ከተከሰሰዉ ሰዉ አንፃር የሚታይ ሆኖ የቅጣት ዉሳኔው የሚወሰነው ዉስን የሆኑ ነገሮችን በመንተራስ ሳይሆን የወንጀሉን ዓይነት፣ ክብደት፣ የተከሳሹን የጥፋተኛነት ደረጃ እና ያለፈ የወንጀል ታሪኩን በማገናዘብ መሆን እንዳለበት ነዉ።

የቀጠለ

- ወጥነት/consistency/፡- በእርግጥ ወንጀል ግላዊ ባህሪ ያለዉ በመሆኑ የአንዱ ምክንያት ለሌላዉ የሚተላለፍ አይደለም።
- ይህ ማለት ግን ወጥ በሆነ መልክ ተመሳሳይ የሆኑ የወንጀል ጉዳዮች አንፃራዊ ልዩነቶች ተቀራራቢ የሆነ ዉሳኔ ሊወሰንባቸዉ አይቻልም ማለት አይደለም።
- ይህ መርህ ፍርድ ቤቶች እንደፈለጉት ወይም እንዳሻቸዉ ቅጣት ከመጣል ገታ በማድረግ ወጥ የሆነ በየጊዜዉ መሻሻል የሚታይበት እንዲሆን ያስችላል።

የቀጠለ

- አድሎ የሌለበት ወይም ፍትሃዊ/Fairness/:- ብዙ ዓይነት የማህበረሰብ ክፍል ባለበት አገር በፍትህ አካላት ዘንድ የሀሳብ ወደ አንድ ወገን ማጋደል እንዳይከሰት የቅጣት አወሳሰን መርህ ክልከላ ያደርጋል ተብሎ ይገመታል። ስለዚህ በዘር፣ በፖሊቲካ፣ በዖታ፣ በኃይማኖት፣ በሀብት ደረጃ እና በመሳሰሉት መነሻ ልዩነት ሳይደረግ ቅጣት መጣል እንዲቻል ያደርጋል ማለት ነዉ።
- ግልፅነት/Transparency/:- ግልፅነትና ተጠያቂነት አብረዉ የሚሄዱ መርሀዎች ናቸዉ።
- ዳኞች ዉሳኔቸዉን በምክንያት ለማስደገፍ ይገደዳሉ። በምክንያት ማስደገፍ ግዴታ ሆኖ በተጨማሪም የሚያቀርቡት ምክንያት ቅጣት ለማክበድም ሆነ ለማቅለል ግልፅነት ያለዉ መሆን ይጠበቃል።

የቀጠለ

- የቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ እነዚህን ምክንያቶች ለአጠቃቀም በሚመች መልኩ በግልፅ በማስቀመጥ ሌሎች የህብረተሰበ አካላትም በግልጽ አይተዉት መገመት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።
- የግልፅነት መርሀዉ የዳኞችን የተጠያቂነት አድማስንም የሚያሰፋ ይሆናል። ።

የቅጣት አይነቶችና አወሳሰን መርሆዎች በኢፌደሪ የወንጀል ህግ

- አንድ ወንጀል የፈጸመ ሰው ወንጀል መፈጸሙ ከተረጋገጠ ሊያርመው ሌሎችን ሊያስተምር ወይም ጥፋተኛው ድጋሜ ወንጀል እንዳይፈጽም የሚያደርገው ቅጣት ይተላለፍበታል።
- ከፍ ብለን ለመመልከት እንደሞከርነው ሊተላለፍ የሚችለውም ቅጣት እንደወንጀሉ ከባድነት ወይም አደገኝነት እንዲሁም የድርጊቱ ፈጻሚ ግላዊ ሁኔታዎች አንጻር የተለያየ ይሆናል።
- ቅጣት በዋናነት በሁለት የሚከፈል ሲሆን ይሔውም ዋና ቅጣትና ተጨማሪ ቅጣት ናቸው።

የቀጠለ

- በመርህ ደረጃ ተጨማሪ ቅጣቶች የሚወሰኑት ለዋናው ቅጣት ተደማሪ ወይም ማሟያ በመሆን ነው።
- ከልዩልዩ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ምንባብ ለመረዳት እንደሚቻለው ተጨማሪ ቅጣቶች የሚባሉት እንደተግሳጽ፣ ወቀሳ፣ ጥፋተኛው ተሸዳዩን ይቅርታ እንዲጠይቅ ማድረግ፣ ከመምረጥ ወይም ከመመረጥ፣ በልዩ አዋቂነት ምስክር ወይም ዋስ ከመሆንና ከመሳሰሉት ህዝባዊ መብቱ፣ ከወላጅነት ወይም ከሞግዚትነት፣ እንዲሁም የሥራ ወይም የንግድ ፈቃድ የሚያስፈልገውን የሙያ፣ የኢንዱስትሪ ወይም የንግድ ሥራ ከመስራት መብት፣ መሻርንና የመሳሰሉትን የሚያካትቱ ናቸው።

የቀጠለ

- ዋና ቅጣት የሚባሉት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 90 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክተው የሚገኙ ሲሆን እነዚህም የገንዘብ መቀጮ፣ የግዴታ ስራ፣ የቀላል እስራት፣ የጽኑ እስራት፣ የድሜ ልክ እስራትና የሞት ቅታቶች ናቸው።
- ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የዚህን ሕግ ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎች፣ ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉን ድንጋጌዎች እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ ነው።

የቀጠለ

- የትኛውም አይነት ቅጣት ሲጣል ወይም ሲወሰን በወንጀል ህጉ የተመለከቱትን የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችና በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በጥንቃቄ ተፈጻሚ በማድረግ መሆን ይኖርበታል።
- የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 4 (9) ላይ እንደተመለከተው መመሪያው በወንጀል ሕግ ስለ ቅጣት አወሳሰን ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥሞ መተርጎም ይኖርበታል በሚል ይደነግጋል።
- በመሆኑም መመሪያውን በአግባቡ ለመረዳት በመጀመሪያ በወንጀል ህጉ የተመለከቱትን የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች መረዳት የሚያስፈልግ ይሆናል።

የቅጣት ማቅለያዎችና ማክበጃዎች

- አንድ ፍ/ቤት የመጨረሻ ቅጣት በሚወስንበት ጊዜ ፍትሃዊነትና ተገቢነት ያለውን ቅጣት ለመጣል ለቅጣቱ አወሳሰን የሚረዱ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።
- እነዚህ ለቅጣት አወሳሰን የሚረዱ ሁኔታዎች በሁለት የሚከፈሉ ሲሆን እነዚህም የቅጣት ማቅለያና ማክበጃዎች ናቸው።
- የቅጣት ማቅለያ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያና ልዩ የቅጣት ማቅለያ በሚል የሚከፈል ሲሆን በተመሳሳይ የቅጣት ማክበጃም ጠቅላላና ልዩ የቅጣት ማክበጃ በሚል የሚከፈል ነው።

የቅጣት ማቅለያዎች

ሀ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ

- ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክኒያት የሚባሉት ሁኔታዎች በመርህ ደረጃ በወንጀል ህጉ ቁጥር 82 ከሀ እሰከ ሰ ተዘርዝረው ይገኛሉ። እነዚህመ ሁኔታዎች
- ሀ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የዘወትር ጠባዩ መልካም እንደሆነና ያጠፋውም በዕውቀት ማነስ፣ ባለማወቅ፣ በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ፤
- ለ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በተከበረና በግል ጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ፍላጐት ወይም ከፍ ባለ ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ ወይም ማሕበራዊ እምነት ተነሳስቶ እንደሆነ፤
- ሐ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው ከፍተኛ የቁሳዊ እጦት ወይም የሕሊና ስቃይ ደርሶበት፣ ከፍ ያለ አደጋ የሚያመጣ ነገር የተቃጣበት መስሎት መሠረት ያለው ፍርሃት አድሮበት ወይም ደግሞ ሊታዘዝለት በሚገባው ወይም በሥልጣኑ ሥር በሚያስተዳድረው ሰው ተፅእኖ ምክንያት እንደሆነ፤

የቀጠለ

- መ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው የተበደለው ሰው ጠባይ ከብርቱ ፈተና ላይ ጥሎት፣ በከባድ ፀብ ቀስቃሽነት ወይም በአፀያፊ ስድብ ምክንያት ወይም ደም ከሚያፈላ ንዴት፣ ስቃይ ወይም ብስጭት ላይ ጥሎት እንደሆነ፤ ወይም ከፍ ያለ አስገዳጅነት ባለው ስሜትን በሚለውጥ ሁኔታ ወይ ምክንያት ባለው የመንፈስ ሁከት ላይ ሆኖ እንደሆነ፤ ወይም
- ሠ/ ወንጀለኛው ወንጀሉን ካደረገ በኋላ በእውነት የተፀፀተ መሆኑን፣ በተለይም በደል ላደረሰበት ሰው አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ፤ ወይም ጥፋቱን በመገንዘብ ራሱን ለፍትህ አካላት በማቅረብ ወይም የወንጀሉ ጥፋት ላደረሰው ጉዳት በተቻለ መጠን በመካስ መፀፀቱን በተግባር አሳይቶ እንደሆነ ወይም ተከስሶ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ያመነ እንደሆነ፤ ነው።

የቀጠለ

- ከነዚህም ምክኒያቶች በተጨማሪ በህግ ባይጸፍም ፍ/ቤቱ አግባብነት አላቸው ብሎ ያመናቸው ሌሎች ምክኒያቶችን በጠቅላላ ማቅለያነት ቅጣትን ለማቅለል ይችላል በሚል በወንጀል ህጉ ቁጥር 86 ላይ የተደነገገ በመሆኑ በዚሁ አግባብ ቅጣት ለማቅለል የሚችል ይሆናል።
- በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሌሎች ሁኔታዎችን ለምሳሌ እንደቤተሰብ አስተዳዳሪ ነኝ የሚሉ ምክኒያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ለማቅለል የሚቻል ይሆናል።

የቀጠለ

- በጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች ወንጀለኞች ቅጣታቸው ሊቀል የሚችልበት አግባብ በወንጀል ህጉ ቁጥር 179 ላይ ተመልክቶ ይገኛል። በዚህ የሕጉ ቁጥር አግባብ
- በሞት ቅጣት ምትክ፣ ከሃያ ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ የሚደርስ ጽኑ እሥራት፤
- በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ምትክ፣ ከአሥር ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የጽኑ እሥራት ቅጣት፤
- የፅኑ እሥራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ በዚህ ቅጣት ምትክ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል መነሻ ሆኖ ከተደነገገው ከአንድ ዓመት ጀምሮ የፅኑ እሥራት ቅጣት፤

የቀጠለ

- መነሻው አንድ ዓመት በሆነ ፅኑ እሥራት ምትክ፣ ከስድስት ወር እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ የቀላል እሥራት ቅጣት፣
- የቀላል እሥራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ በዚህ ቅጣት ምትክ፣ ከአስር ቀን የማያንስ የቀላል እሥራት ቅጣት፤
- ከአስር ቀን በማያንስ የቀላል እሥራት ቅጣት ምትክ የግዳጅ ሥራ ወይም መቀጫ፣ ይወስናል።

የቀጠለ

- ከጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክኒያቶች (82/86) በተጨማሪ በህጉ ልዩልዩ ድንጋጌዎች በአንቀጽ 179 መሰረት ፍ/ቤቶች እንዲያቀሉ ይችላሉ በሚል በተደነገገ ጊዜ ቅጣት የሚቀልበት አግባብ ከላይ ባየነው መልኩ ይሆናል።
- ከነዚህም ድንጋጌዎች መካከል አንቀጽ 27 (3) ሙከራን በተመለከተ፣ 28 (1) መጸጸትን አስመልክቶ፣ 36 (3) በማነሳሳት ለተከሰሰ ሰው፣ 37 (3) መሰረት በአባሪነት ለተከሰሰ ሰው፣ 56 (2)/176 መሰረት ወጣት ጥፋተኛን በተመለከተ፣ 372 (3) በሀሰተኛ ገንዘቡ የደረሰው ጉዳት አነስተኛ ከሆነ፣ 617 በስድብና ማዋረድ የተከሰሰ ሰው ቃሉን ያነሳና የተጸጸተ መሆኑን ለፍ/ቤቱ በጽሁፍ ወይም በቃል የገለጸ እንደሆነ ቅጣት የሚቀልበት፣የሚጠቀሱ ምሳሌዎች ናቸው።

የቀጠለ

- የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 7 በሰመቁ 34521 በሰው መግደል ሙከራ ወንጀል (1949ኙ የወንጀል ህግ አንቀጽ 523) በሙከራ ወንጀል ቅጣት በምን መለኩ ሊቀል የሚገባ እንደሆነ የወሰነበትን ማየት ይቻላል።
- በዚህ ውሳኔ መሰረት የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከላይ በተመለከተው ድንጋጌ የተከሰሰና ጥፋተኛ የተባለ ሰውን በ6 ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን ይህንኑ ውሳኔ የወንጀል ህጉን የቅጣት አወሳሰን መርህ አልጠበቀም በሚል በ1 አመት ጽኑ እስራት የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀጥቶታል።

የቀጠለ

- እዚህ ላይ ትንቃቄ ሊወሰድበት የሚገባው ነጥብ፣ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 82 (1) ላይ የተመለከቱት የቅጣት ማቅለያዎች ሲገኙ ሁልጊዜም በቅጣት ማቅለያነት ይወሰዳሉ የሚባሉ እንዳልሆነ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በማቅለያነት የማይጠቅሙት በወንጀል ህጉ ቁጥር 82 (2) ላይ እንደተመለከተው በልዩ የህጉ ክፍል ድንጋጌ በማቅለያነት ተመልክተው የተገኙ እንደሆነ ነው።
- ይህንንም በምሳሌ ለመመልከት ያህል በጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክኒያትንት በአንቀጽ 82 (1) መ ላይ የተመለከተውን ብንወስድ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው የተበደለው ሰው ጠባይ ከብርቱ ፈተና ላይ ጥሎት፣ በከባድ ፀብ ቀስቃሽነት ወይም በአፀያፊ ስድብ ምክንያት ወይም ደም ከሚያፈላ ንዴት፣ ስቃይ ወይም ብስጭት ላይ ጥሎት እንደሆነ፤ ወይም ከፍ ያለ አስገዳጅነት ባለው ስሜትን በሚለውጥ ሁኔታ ወይ ምክንያት ባለው የመንፈስ ሁከት ላይ ሆኖ እንደሆነ፤ በህጉ መሰረት ቅጣት ሊቀልለት የሚቸል ይሆናል።

የቀጠለ

- ነገር ግን ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለው በወንጀል ህጉ ቁጥር 541 ለ በቀላል የሰው ግድያ ቢሆን በዚሁ የድንጋጌው ማቋቋሚያ ተመሳሳይነት ያላቸው ሁኔታዎች በማቅለያነት የተመለከቱ በመሆኑ በድጋሜ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 82 (1) መ መሰረት ለማቅለል የሚቻል አይሆንም።
- ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 12 በሰበር መዝገብ ቁጥር **59356** በሰጠው ውሳኔ በአንቀጽ **540** በተራ የሰው መግደል ወንጀል የተከሰሰ ሰው ድርጊቱ የተፈጸመው በድንገተኛ አጋጣሚ ነው የሚለው የወንጀል ድንጋጌው ማቋቋሚያ በመሆኑ በህጉ ቁጥር **82 (2)** መሰረት እንደማቅለያ ሊያዝ የሚገባው እንዳልሆነ ውሳኔ ሰጥቷል።

ለ ልዩ የቅጣት ማቅለያዎች

- ከወንጀል ህጉ ቁጥር 83 (1) ለመረዳት እንደሚቻለው ልዩ የቅጣት ማቅለያዎችን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡
- የመጀመሪያው ከላይ በተጠቀሰው የህጉ ድንጋጌ ወንጀለኛው ሕግን የሚቃረን ተግባር ያደረገው፣ በተለይም ወንጀል ማድረጉንና ወንጀለኛውን እያወቀ ለፍርድ ባለሥልጣን የማስታወቅ ግዴታውን ያልፈፀመው ወይም መስጠት የሚገባውን እርዳታ ያልሰጠው፣ ሐሰተኛ መግለጫ፣ ምስክርነት ወይም መረጃ የሰጠው ወይም ወንጀለኛው ከክስ ወይም ከቅጣት አፈፃፀም እንዲያመልጥ የረዳው ራሱን፣ የቅርብ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዱን ወይም በተለይ ጥብቅ በሆነ ወዳጅነት የተሳሰረውን ሰው ለቅጣት፣ ለውርደት ወይም ለከባድ አደጋ ላለማጋለጥ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በመሰለው ቅጣት የሚያቀልበት አግባብ ነው፡፡
- እንዲህ አይነቱ የቅጣት ማቅለያ ተቀባይነት የሚኖረው ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ወይም ጥብቅ የሆነ ወዳጅነት ግንኙነት ምክንያት በቂ መሆኑን ማረጋገጥ የቻለ እንደሆነ ነው፡፡

የቀጠለ

- ከቅጣት ማቅለያ ባለፈም በህጉ አንቀጽ 83 (2) ላይ እንደተመለከተው ወንጀለኛው የሚጠየቅበት ጥፋት ወይም ከባድ ያልሆነና ይህ የተባለው ዝምድና ወይም በወዳጅነት የተሳሰረ ግንኙነት እጅግ ጥብቅ በመሆኑ የነገሩ ሁኔታ የሚያስጨንቅ ስሜት ያሳደረበት በመሆኑ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ ወንጀለኛውን በማስጠንቀቅ ወይም በወቀሳ ብቻ በማለፍ ሊወሰን ከሚችለው ሌላ ቅጣት ነፃ ሊያደርገው ይችላል (አንቀጽ 122)።
- በዚህ አግባብ ከቅጣት ነጻለማድረግ ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለው ከባድ ባልሆነ የወንጀል ድርጊትና ዝምድና ወይም በወዳጅነት የተሳሰረ ግንኙነት እጅግ ጥብቅ በመሆኑ የነገሩ ሁኔታ የሚያስጨንቅ ስሜት ያሳደረበት በመሆኑ እንደሆነ፤የሚሉት ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል።

የቀጠለ

- እንዲህ አይነቱ የዝምድና ወይም የጥብቅ ወዳጅነት እንደማቅለያ ወይም ከቅጣት ነጻ ለማድረግ የማይቻልባቸው ልዩ ሁኔታዎች በህጉ ቁጥር 83 (3) ላይ ተደንግገዋል። በዚህም መሰረት ከፍ ያለ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ በህጉ አንቀጽ 254 (4)፣ 335 (3) እና 682 (5) የተመለከቱት ወንጀሎች ዝምድናና ወይም ጥብቅ ወዳጅነትን መሰረት በማድረግ ቅጣት ማቅለያ የሚሆኑ አይሆኑም።

የቀጠለ

- በወንጀል ህጉ ቁጥር 83 ከተመለከቱት የልዩ የቅጣት ማቅለያዎች በተጨማሪ በልዩ የህጉ ክፍል ድንጋጌዎች ፍ/ቤቱ በመሰለው ለማቅለል ይችላል በሚል የተደነገገ እንደሆነ ነው። ልዩ ልዩ የህጉን ድንጋጌዎች ስንመለከት በዚህ አግባብ ተደንግገው ይገኛሉ፣ ለምሳሌ ብንመለከት 28 (2) 29፣ 49 (1)፣ 76፣ 79 (1)፣ 81 (2)፣ 544 (1)፣ 550፣ 652 (2)፣ የሚጠቀሱ ናቸው።

የቀጠለ

- ፍ/ቤቱ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክኒያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣት የሚያቀልበት ደንብ በህጉ አንቀጽ 180 ላይ ተመልክቷል። ፍ/ቤቱ ይህንን የቅጣት ማቅለያ መሰረት አድርጎ ቅጣት ሲያቀል የዚህ ሕግ ልዩ ክፍል በሚደነግገው የቅጣት ዓይነት ወይም መነሻ ቅጣት ሳይወሰን መነሻ ከሆነው ቅጣት ዝቅ አድርጎ ወይም ቀለል ያለ ሌላ ዓይነት ቅጣት ተክቶ ለመወሰን ይችላል።
- ነገር ግን ፍርድ ቤቱ የሚወስነው ማናቸውም ዓይነት ቅጣት በዚህ ሕግ ጠቅላላ ክፍል ለየቅጣቱ ዓይነት ከተደነገገው መነሻ ዝቅ ሊል አይችልም /አንቀጽ (90፣ 106 እና 108)።
- በዚህም መሰረት የጽኑ እስራትን በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ወይም የሞት ቅጣትን በጽኑ እስራት ወይም በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ለመቅጣት የሚችል ይሆናል።

የቀጠለ

- ይሁንና ፍ/ቤቱ ለመረጠው የቅጣት አይነት በጠቅላላ ክፍሉ ለቅጣቱ አይነት መነሻ ከተደረገው ቅጣት ወርዶ መቅጣት የሚችል አይሆንም። ለምሳሌ ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለው በጽኑ እስራት ለማስቀጣት በሚችል ወንጀል ቢሆን ፍ/ቤቱ ቀላል እስራት ወይም መቀጮ ለመቅጣት ቢወስን ቀላል እስራቱን ከአስር ቀን ሳይወርድ (106) እንዲሁም መቀጮውን ከአስር ብር ሳይወርድ (90) መቅጣት የሚችል ይሆናል።

የቅጣት ማክበጃዎች

ሀ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች

- ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክኒያቶች በወንጀል ህጉ ቁጥር 84 (1) ከሀ እስከ ሰ ተዘርዝረዋል። እነዚህን ምክኒያቶች ለመመልከት ያህል
- ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በከሐዲነት ወይም በወስላታነት፣ ወራዳነትን ወይም መጥፎ አመልን በሚያሳይ ምቀኝነት፣ ጥላቻ፣ ስግብግብነት፣ መጥፎ ነገርን ለመሥራት ወይም ሰውን ለመጉዳት ፍጹም ፈቃደኛ በመሆን፣ ወይም በተለየ ክፋት ወይም ጨካኝነት እንደሆነ፤
- ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው ሥልጣኑን፣ ተግባሩን ወይም የተጣለበትን እምነት ወይም ላፊነት ያለአግባብ በመገልገል እንደሆነ፤
- ወንጀለኛው በቀድሞ ጥፋተኛነቱ፣ ወንጀልን ማድረግ ሙያ ወይም ልማድ አድርጐ መያዙ፣ ወይም የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፣ ጊዜ፣ ቦታና የአፈጻጸሙ አኳኋን፣ በተለይም በሌሊት ወይም በሽብር ወይም በሁከት ለአደጋ ሽፋን ወይም በጦር መሣሪያ ወይም በሌላ አደገኛ መሣሪያ ወንጀሉን በማድረግ የተለየ አደገኛነቱን አሳይቶ እንደሆነ፤

የቀጠለ

- ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው ወንጀል ለመፈፀም በተደረገ ስምምነት መሠረት ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ወይም ወንጀል ለመፈፀም ከተቋቋመ ቡድን ጋር በመስማማት ወይም አባል በመሆን ይልቁንም እንደወንጀል ቡድን ሹም፣ አደራጅ ወይም መሪ በመሆን እንደሆነ፤ ወይም
- ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በዕድሜው፣ በጤንነቱ፣ በኑሮው ወይም በሥራው ሁኔታ ልዩ ጥበቃ በሚያሻው ሰው ላይ በተለይም ለመከላከል አቅም በሌለው፣ መንፈሰ ደካማ፣ በሽተኛ ወይም የአካል ጉዳተኛ፣ እሥረኛ ወይም በቅርብ ዘመዱ ላይ ወይም የበላዩ ወይም የበታቹ በሆነ ሰው ላይ፣ በሕግ በተቋቋመ ባለሥልጣን ወይም የሥራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ በአንድ የሕዝብ አገልጋይ በሆነ ሠራተኛ ላይ እንደሆነ፤ ነው።

የቀጠለ

- ከነዚህም ምክኒያቶች በተጨማሪ በህጉ ቁጥር 86 መሰረት ፍ/ቤቱ እንደጠቅላላ ማክበጃ ሊወሰዱ ይገባል የሚላቸውን ምክኒያቶች ተጠቅሞ ቅጣትን ለማክበድ የሚችል ይሆናል።
- በዚህ አይነቱ የቅጣት ማክበጃ ቅጣት የሚከብድበት ሁኔታ በህጉ ቁጥር 183 ላይ ተደንግጓል። በዚህም ድንጋጌ መሰረት ፍ/ቤቱ በጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች ቅጣት ለማክበድ የሚችለው በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል በተመለከተው አግባብነት ባለው ድንጋጌ ከተወሰነው ቅጣት ጣራ ሳያልፍ ሊሆን ይገባል።
- በመሆኑም በጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ቅጣት ሊከብድ የሚችለው ወንጀለኛው ጥፋተኛ ለተባለበት የወንጀል ህጉ ድንጋጌ ጣራ ድረስ ብቻ እንደሆነና ከጣራው በላይ አሳልፎ መቅጣት የሚቻል አይሆንም ማለት ነው።

የቀጠለ”

- ነገር ግን በአንቀጽ 84 (1) ላይ ከተዘረዘሩት የቅጣት ማክበጃ ምክኒያቶች መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ምክኒያቶች ወንጀለኛው ጥፋተኛ ለተባለበት ድንጋጌ በማቋቋሚያነት ወይም በማክበጃነት የተወሰዱ ከሆነ እነዚህን ምክኒያቶች መሰረት በማድረግ ቅጣትን ለማክበድ እንደማይቻል የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (2) ይነግረናል።
- ይህንንም በምሳሌ ብንመለከት የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 881/07 አንቀጽ 9 እንደሚደነግገው በስልጣን አላግባብ በመገልገል የማይገባ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያስገኘ እንደሆነ በሚል ቅጣት የሚያስቀምጥ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ ለተባለ ሰው በወንጀል ህጉ ቁጥር 84 (1) ለ የተመለከተውን በማክበጃነት ለማቅረብ የሚቻል አይሆንም

የቀጠለ

- በሌላ በኩል በቅጣት ማክበጃነት የቀደመ የወንጀል ርኮርድን በተመለከተ 539 (2) ማየት የሚቻል ይሆናል።በተመሳሳይ የወንጀል ህጉን ቁጥር 671 እና የመሳሰሉትን ድንጋጌዎች መጥቀስ ይቻላል።

ለ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክኒያቶች

- በወንጀል ህጉ አንቀጽ 85 እንደተነገረው ሁለት አይነት ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክኒያቶች አሉ። እነዚህም የቅጣት ማክበጃ ምክኒያቶች ተደራራቢ ወንጀልን መፈጸምና ደጋጋሚነት ናቸው።

1 የተደራራቢ ወንጀል ምንነትና የቅጣቱ አወሳሰን አግባብ

- የተደራራቢ ወንጀሎች ምንነት በወንጀል ህጉ ከቁጥር 60-66 እንዲሁም የቅጣቱ አወሳሰን አግባብ ከቁጥር 184-187 ላይ ተደንግጎ ይገኛል። ከወንጀል ህጉ ቁጥር 60 ለመረዳት እንደሚቻለው 3 አይነት የተደራራቢ ወንጀሎች እንዳሉ ነው።

1.1 ግዙፋዊ መደራረብ *(Material concurrence)*

- የመጀመሪያው አይነት ተደራራቢ ወንጀል ግዙፋዊ መደራረብ ***(Material concurrence)*** የምንለው ሲሆን ይህም በህጉ ቁጥር ***60 ሀ/64*** ላይ ተደንግጎ ይገኛል።
- በነዚህ ድንጋጌዎች መሰረትም እንዲህ አይነቱ ተደራራቢ ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ማናቸውንም ዓይነት ግዙፍ ወንጀሎችን አከታትሎ ያደረገ እንደሆነ ነው።
- በዚህም ሁለትና ከሁለት በላይ ወንጀሎች መሆኑ፣ ተመሳሳይ ወይም የተለያዩ ወንጀሎች መሆናቸውና እነዚህ ወንጀሎች የተፈጸሙት ተከታተለው መሆናቸው የሚሉት ግዙፋዊ ተደራራቢ ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት መሟላት የሚገባቸው ቅድመሁኔታዎች ናቸው።

የቀጠለ

- ስለዚህ እንዲህ አይነቱ ተደራራቢ ወንጀል በአንድ ድርጊት የሚፈጸም ሳይሆን በተለያየ ድርጊት ሆኖ አፈጻጸሙም ተከታትሎ ነው።
- ተከታትሎ የሚለው አንድን ወንጀል ከፈጸመ በኋላ ወዲያው ወይም ይሄው ቀደም ብሎ የፈጸመውን ወንጀል መሰረት አድረጎ በህግ ከመቀጣቱ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ የሚፈጽመው የወንጀል ድርጊት ሊሆን ይችላል።

የቀጠለ

- በግዙፋዊ የተደራራቢ ወንጀል ጊዜ ቅጣት የሚጣልበት አግባብ በአንቀጽ 64 እንደተመለከተው በወንጀል ህጉ ቁጥር 184እንደሚሆን ነው። በዚሁ ድንጋጌ እንደተመለከተው ቅጣቱ በሁለት መልኩ ማለትም በማጠቃለልና በመደመር የሚከብድ ይሆናል።
- ማጠቃለልን በተመለከተ በወንጀል ህጉ ቁጥር 184)1) ሀ መሰረት በግዙፋዊ ተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛየተባለ ሰው ጥፋተኛ ከተባለባቸው ወንጀሎች መካከል በአንዱ የሞት ወይም የድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት /አንቀጽ 106/108 ቢፈረድበት ይህ ቅጣት ከመቀጮ ቅጣት ውጪ የሆኑትን የሥራት ቅጣቶች አጠቃሎ የሚይዝ ይሆናል።

የቀጠለ

- በሌላ በኩል ቅጣቱ ከፍ ብለን በተመለከትነው አግባብ የሚጠቃለል ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ በዚሁ ህግ ቁጥር 184 (1) ለ መሰረት ለእያንንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም ይደመራል። ነገር ግን ለቅጣቱ አይነት በጠቅላላው ክፍል ከተመለከተው ጣራ በላይ ለመቅጣት አይቻልም።
- በዚህ ጊዜ የጽኑና የቀላል እስራት ተቀላቅሎ በሚገኝበት ጊዜ የቀላሉ እስራት በግማሽ ቀንሶ ወደጽኑ እስራት በመቀየር ደምሮ መቅጣት የግድ ይላል። ።
- በመቀጨ ቅጣት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣት በመወሰን በህጉ ከተቀመጠው ጠቅላላ ክፍል ጣሪያ ሳያልፍ በመደመር መቅጣት (184 (1)/መ

ጣምራ ተደራራቢ ወንጀሎች (notional concurrence)

- ሁለተኛው የተደራራቢ ወንጀል አይነት ጣምራ ተደራራቢ ወንጀል የምንለው ሲሆን ይኼውም በወንጀል ህጉ ቁጥር 60 ለ እና 65/66 ላይ ተደንግጎ እናገኘዋለን።
- ጣምራ ተደራራቢ ወንጀሎችን በሁለት ከፍሎ መመልከት የሚቻል ሲሆን የመጀመሪያው በአንቀጽ 60 ለ እና 65 ላይ እንደተደነገገው በአንድ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆኑ የወንጀል ድንጋጌዎችን ተላልፎ መገኘት የሚለው ነው።
- ለምሳሌ አንድ ሰው የሚስቱን እህት በአደባባይ ላይ ቢደፍራት ድርጊቱ አንድ ቢሆንም የተላለፋቸው የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች አስገድዶ መድፈርን፣ 620 (1)፣ ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ተግባርን መፈጸም 639፣ ዝሙት መፈጸም 652 እንዲሁም ከዘመድ ጋር ግበረ-ስጋ ግንኙነት መፈጸም 654 በመተላለፉ በሁሉም ድንጋጌዎች የሚከሰስና በወንጀል ህጉ መሰረት የሚፈረድበት ይሆናል።

የቀጠለ

- በዚህ የጣምራ ጠደራራቢ ወንጀል አይነት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ቅጣቱ የሚጣልበት አግባብ በህጉ ቁጥር 187 (1) ላይ ተደንግጎ ይገኛል።
- በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ፍ/ቤቱ የጉዳዩን አካባቢ ሁኔታዎች ሲመረምር በተለይም ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ሕግ መጣሱን ወይም ግልፅ የሆነ መጥፎ ጠባይ ማሳየቱን ባመነ ጊዜ በአንቀጽ 184 በተመለከተው መሠረት ቅጣቱን አክብዶ መወሰን ይችላል።
- ነገር ግን ፍ/ቤቱ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች የሌሉ መሆናቸውን ካመነ አግባብ ባለው የሕግ ድንጋጌ ለከባዱ ወንጀል የተደነገገውን ከፍተኛ የቅጣት ወሰን ሳያልፍ ቅጣቱን ይወስናል።

የቀጠለ

- ሌላኛው ጣምራ ተደራራቢ ወንጀል በወንጀል ህጉ ቁጥር 60 ለ እና 66 ላይ ተደንግጎ የሚገኘው ነው።
- በነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በአንድ ድርጊት ልዩ ልዩ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን በጦር መሳሪያ፣ በአደገኛ መሳሪያ፣ በእሳት፣ በሚፈነዳ ነገር፣ በመርዝ፣ በሚያፈዝ መድኃኒት በመገልገል ወይም በሰው ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ አንድ የተወሰነ ወንጀል ሲደረግ የሰውን ህይወት እንደማሳለፍ ወይም በሰው አካል ወይም በሰው ንብረት ላይ ጉዳት እንደማድረስ የመሳሰለ ሌላ ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ ነው።
- በህጉ አንቀጽ 66 ላይ እንደተመለከተው ፍ/ቤቱ በዚህ አግባብ ጥፋተኛ ያለውን ሰው እንደጥፋተኛው የሀሳብክፍል ቅጣቱን በሁለት መልኩ ሊወስን ይችላል።

የቀጠለ

- የመጀመሪያው በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (1) ሀ፣ ለ እና ንዑስ ቁጥር (2) መሰረት ቢያንስ የመጀመሪያውን ወንጀል አስቦ የፈጸመው ከሆነ ተከታዩ ወንጀል ታስቦም ሆነ በቸልተኝነት የተፈጸመው ፍ/ቤቱ በወንጀል ህጉ ቁጥር 187 (2) ሀ እና ሐ/184 መሰረት ቅጣቱን የሚወስን ይሆናል።
- ይህም ማለት እንደነገሩ ሁኔታ በማጠቃለል ወይም በመደመር ቅጣቱ የሚወሰን ይሆናል ማለት ነው።
- ነገር ግን የመጀመሪያው ወንጀል በቸልተኝነት የተፈጸመ ሆኖ ሌላ በቸልተኝነት የተፈጸመ ወንጀል እንደሆነ በህጉ አንቀጽ 187 (2) ለ መሰረት በሕጉ ልዩ ክፍል ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ሳይታለፍ ቅጣት ይወሰንበታል።
- በመሆኑም እንዲህ አይነቱ በቸልተኝነት የሚፈጸም ጣምራ ወንጀል በመደመር ወይም በማጠቃለል ሳይሆን ዝቅተኞቹ ወንጀሎች ለከባዱ ወንጀል በማክበጃነት በመውሰድ ቅጣቱ የሚከብድ ይሆናል።

በአንድ ድርጊት ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ ተመሳሳይ የሆነ ወንጀል መፈጸም

- ሶስተኛው የተደራራቢ ወንጀል አይነት በህጉ ቁጥር 60 ሐ ላይ የተመለከተው ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ መሰረት በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት ያደረገው ወንጀል አንድን የሕግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ፤ ነው።
- ይህ አይነቱ ተደራራቢ ወንጀል በአንድ ድንጋጌ ሊወድቅ የሚችል ሆኖ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ላይ በአንድ ድርጊት ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ነው።
- ለምሳሌ ቦንብ በመወርወር ሶስት ሰዎችን ቢገድል ለእያንዳንዱ ሰው ክስ ይመሰረትበታል፤ ቅጣቱም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 184 (2) አግባብ በሌላ አኳኋን እስካልተደነገገ ድረስ በ184 (1(መሰረት ቅጣቱ የሚሰላ ይሆና።

ከፍርድ በኋላ የተደራቢ ወንጀል መኖር መታወቅ

- አንድአንድ ጊዜ አንድ ወንጀለኛ አድራጊ በተደራራቢ ወንጀል መከሰስና መቀጣት ሲገባው ተደራቢው ወንጀል ባለመታወቁ ምክኒያት በታወቀው ወይም በታወቁት የወንጀል ድርጊቶች ይከሰስና ይቀጣል።
- ይህንንም ቅጣትበመፈጸም ላይ ሳለ ወይም ከፈጸመ በኋላ ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት የፈጸመው ሌላ ተደራራቢ ወንጀል መኖሩ ከታወቀ የዚህ ዘግይቶ የታወቀው ተደራቢ ወንጀል የቅጣት አወሳሰኑ በወንጀል ህጉ ቁጥር 186 ላይ ተደንግጓል።
- በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት ፍ/ቤቱ ጥፋተኛው በፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ ቅጣቱን መወሰን ይኖርበታል።

የቀጠለ

- በዚህም መሰረት ለምሳሌ ጥፋተኛው በተለያየ ጊዜ የፈጸማቸው ሁለት የሰው መግደል ወንጀልና ሌላ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ቢፈጽምና ነገር ግን የአስገድዶ መድፈ ወንጀል ሳይታወቅ ቀርቶ በሁለቱ የሰው ግድያ ወንጀሎች 23 አመት የጽኑ እስራት ተፈርዶበትና ቅጣቱን በመፈጸም ላይ ሳለ ይሄው የአስገድዶ መድፈሮ ወንጀል ቢደረስበትና ፍ/ቤቱም በዚሁ ወንጀል ጥፋተኛ ቢለው በዚህ ወንጀል ሊቀጣ የሚችለው ከፍተኛው ቅጣጥ 2 አመት ይሆናል።
- ምክኒያቱም ለጽኑ እስራት ከፍተኛው ቅጣት 25 አመት በመሆኑና የአስገድዶ መድፈሩ ወንጀል አብሮ ከሰው ግድያ ወንጀሎቹ ጋር አብሮ ቢታይ ኖሮ በህጉ ቁጥር 184 (1) ለ መሰረት ከ25 አመት በላይ ሊፈረድበት ስለማይችል ነው።
- እንዲሁም ተጣምረው ሊታዩ የሚገባቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በተለያዩ ፍ/ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ የጠቅላላ ቅጣቱ አወሳሰን ከፍ ብለን በተመለከትናቸው ድንጋጌዎች መሠረት መሆን እንዳለበት የወንጀል ህጉ ቁጥር 186 (3) ይደነግጋል።

የቀጠለ

- በመሆኑም በአንድ ጊዜም ሆነ በተለያየ ጊዜ ወይም ተጣምረውም ሆነ ሳይጣመሩ የተደራራቢ ወንጀሎች የቅጣት አሰላል ተመሳሳይነት ሊኖረው የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።
- ይህንኑ በተመለከተ የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 16 መዝገብ ቁጥር 96503 በተለያየ ጊዜና መዝገቦች የተለያዩ ቅጣቶች በአንድ ተከሳሽ ላይ በሚወሰንበት ጊዜ ተከሳሹ ይጣመርልኝ ብሎ በሚጠይቅበት ጊዜ በተለያዩ ፍ/ቤቶች የተወሰኑበት ቅጣቶች ለጠቅላላው የቅጣቱ አይነት ከተመለከተው የቅጣት ጣሪያ ሳያልፍ ተደምረው የሚፈፀሙ መሆን ስለሚኖርባቸውና የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ግን እንደገና በድጋሚ የሚታዩበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ውሳኔ ሰጥቷል።

ልዩ ሁኔታዎች

- በአንቀጽ 60 ለተመለከቱት ተደራራቢ ወንጀሎች ልዩ ሁኔታዎች በአንቀጽ 61 እና 63 ላይ ተደንግገዋል።
- በአንቀጽ 61 (1) ላይ እንደተመለከተው በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፍኑ ሲሆን፣ አድራጊው ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም በሚል ተደንግጓል።
- በዚህም ድንጋጌ 3 ቅድመሁኔታዎች ማለትም ወንጀሉ የተፈጸመው በአንድ መብት ላይ መሆኑ፤ በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት የተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም የወንጀል ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ መሆናቸው የሚሉት ተሟልተው ሊገኙ የሚገቡ ናቸው።

የቀጠለ

- ለምሳሌ አንድ ሰው ለመግደል በማሰብ ሟችን በመደብደብ አይኑን በማጥፋት እግሩን በመቁረጥ ቢገድለው በሰው አካል ላይና ጤና ላይ ከባድ ጉዳት በማድረስ (555) እና በከባድ የሰው መግደል ወንጀል (539) ሊከሰስና ሊቀጣ አየገባውም። ሊከሰስና ሊቀጣ የሚገባው በአንቀጽ 539 መሆን ይኖርበታል።
- ሌላኛው ልዩ ሁኔታ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 61 (2) ላይ የተደነገገው ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ መሰረት በሕግ በተጠበቀ በዚያው በአንድ መብት ላይ ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተደረጉ የወንጀል ተግባሮች በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኝነት በተደረጉ ጊዜ እንደ አንድ ወንጀል ይቆጠራሉ።
- ወንጀል አድራጊው ለዚሁ እንደ አንድ ወንጀል ለተቆጠረው እንጂ ተደጋግሞ ወይም ተከታትሎ ለተፈፀመው ለእያንዳንዱ ድርጊት የሚቀጣ አይሆንም።

የቀጠለ

- በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት የፈጸመ መሆኑና በዚያው አንድ መብት ላይ ተከታትሎ ወይም ተደጋግሞመፈጸሙ የሚሉት ሁለት ቅድመሁኔታዎች ለዚህ ልዩ ሁኔታ ተፈጻሚነት መሟላት የሚገባቸው ናቸው።
- ለምሳሌ ለአንድ ወር ያህል ከቀጣሪዋ መቶ ብር ስትሰርቅ የነበረች ካሸር ቢደረስባት በአንድ ክስ እንጂ ሰላሳ ክስ ቀርቦባት የምጥቀጣ አይሆንም።

የቀጠለ

- የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (3) እንደደነገገው ማንኛውም ሰው የተወሰነ ወንጀል ለማድረግ ሀሳብ አለው ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ፣ በተለይም የማይገባውን ብልፅግና ለማግኘት በንብረት ላይ ወንጀል አድርጎ እንደሆነ ወይም የሃሰት ገንዘብ ሰርቶ እንደሆነ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጎ እንደሆነ ወይም ሃሰተኛ ሰነድ ሰርቶ ወይም ተጠቅሞበት እንደሆነ፤ የመጀመሪያውን የጥፋት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ሲል መሰረታዊ ከሆነው ወንጀል በኋላ አከታትሎ ያደረገው ድርጊት ከቀድሞው አሳቡና ሊደርስበት ካቀደው ግቡ ጋር የተያያዘ ሆኖ ዋናው ወንጀል ይጠቃለላል።

የቀጠለ

- ለምሳሌ አንድ ሰው ሀሰተኛ የሆነ መንጃ ፍቃድ አዘጋጅቶ መኪና ሲነዳ ቢገኝ ይህ ሰው ሊቀጣ የሚገባው ሰነዱን በሀሰት በማዘጋጀቱ (375) እንጂ ሀሰተኛ የሆነ ሰነድ በመገልገል (378) ድንጋጌ በተደራቢነት የሚቀጣ አይሆንም።
- ነገር ግን ይህ አይነቱን ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የማታለል ወንጀል የተፈጸመ ከሆነ ወንጀለኛው በወንጀል ህጉ ቁጥር 699 መሰረት በተደራራቢ ወንጀል የሚጠየቅ ይሆናል። ለምሳሌ አንድ ሰው የሀሰተኛ የወራሽነት ሰነድ በመስራት ይህንኑ ሀሰተኛ የሆነ ሰነድ በመገልገል የማይገባውን ውርስ ቢወርስ ሀሰተኛ የሆነ ሰነድን በማዘጋጀት (375) እና ሀሰተኛ የሆነ ሰነድን በመገልገል የማታለል ወንጀልን በመፈጸሙ (692) መሰረት በተደራራቢ ወንጀሎች የሚከሰስና የሚቀጣ ይሆናል።

የቀጠለ

- በተመሳሳይ በወንጀል ህጉ ቁጥር 388 መሰረት ሀሰተኛ ሰነድን በመገልገል የእምነት ማጉደል/ማታለል ወንጀል የተፈጸመ ከሆነ የወንጀል ህጉ ቁጥር 385 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እና) በእምነት ማጉደል (675/676) ወይም በማታለል ወንጀሎች በተደራራቢነት የሚቀጣ ይሆናል።

የቀጠለ

- ይሁንና ወንጀል አድራጊው በአንቀጽ 61 ከንዑስ ቁጥር (1)-(3) የተመለከተውን ጠባይ የያዘ ወንጀል ካደረገ በኋላ ቀድሞ አድርጐት ከነበረው ወንጀል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሌላ ወንጀል በአዲስ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት እንደገና ቢያደርግ፣ ወንጀሉን ያደረገው ቀድሞ በድሎት በነበረው ሰው ወይም በሕግ የተጠበቀው በዚያው መብት ላይ ቢሆን እንኳን፣ ይህ አዲስ ወንጀል ስለሆነ ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ 184 ስለተደራራቢ ወንጀሎች በተደነገገው መሠረት ቅጣቱን ያከብዳል።
- ይህም የሆነበት ምክኒያት የወንጀል ህጉ መቅጣት የሚፈልገው የወንጀል አድራጊውን ሀሳብ በመሆኑ ነው።

የቀጠለ

- የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 12 ሰበር መዝገብ ቁጥር 67947 ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሰጠው ውሳኔ ተከሳሹ በሁለት ክሶች ይሄውም በአንድ ቀን ልዩነት ለአንድ ሰው በሰጣቸው ሁለት ስንቅ የሌላቸው ቼኮች ሊከሰስና ሊቀጣ የሚገባው በሁለት ክሶች ነው በሚል ውሳኔ ሰጥቷል።
- ለዚህም በምክኒያትነት የተቀሰው ድርጊቱ የተፈፀመው በአንድ ቀን ልዩነት ከመሆኑም በላይ የተሠጠበት ዓላማም ለተለያዩ ይሄውም የድርጅቱን ደረጃ ለማሣደግና ለዕዳ መክፈያ በሚል በመሆኑ በአንድ የወንጀል ሃሣብ የተፈጸመ ድርጊት ነው የሚያሠኝ ሣይሆን በወ.መ.ሕግ ቁ 62 መሠረት በአዲስ ሃሣብ እንደሠራው ይቆጠራል በሚል ነው።

የቀጠለ

- በአንቀጽ 63 የተመለከተው ሌላው ልዩ ሁኔታ የተዛመዱ ወንጀሎች በተፈጸሙ ጊዜ ያለውን ጥፋተኝነት የሚመለከት ነው።
- በዚህ ድንጋጌ መሰረት ወንጀል አድራጊው ሌላ ወንጀል ለማድረግ እንዲመቸው ወይም ቀደም ሲል ላደረገው ወንጀል ከለላ እንዲሆነው ሌላ ወንጀል ያደረገ እንደሆነ እና ይህንን ሊፈፅም ያሰበውን ዋና ወንጀል ቢያንስ ሞክሮ እንደሆነ፤ ሕጉ እንደ አንድ ከባድ ወንጀል የሚቆጥረው ካልሆነ በቀር በተደራረቡ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ስለማክበድ (አንቀጽ 184) የተደነገገው የቅጣት አወሳሰን ደንብ ይፈጸምበታል።

የቀጠለ

- ለምሳሌ አንድን ሴት ለማግባት በማሰብ የጠለፈ ሰው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በተጠላፊዋ ላይ ቢፈጽምባት በመጥለፍና በአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች በተደራራቢነት ተጠያቂ ይሆናል አንቀጽ (687 (2)።
- ነገር ግን አንድ ሰው ሲገድል የተመለከተው ሰው ማስረጃ እነዳይሆንብኝ በሚል ቢገድለው በተደራራቢ ወንጀል ሳይሆን በአንቀጽ 539 (1)/ሐ መሰረት እንዲሁም አንድ ባንክ ለመዝረፍ የሄዱ ዘራፊዎች የባንኩን ጥበቃዎች ለመዝረፍ ይመቻቸው ዘንድ ቢገድሏቸው በአንቀጽ 671 (2) መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ።

2 ደጋጋሚነት

- የአንድ ወንጀል አድራጊ የቀደመ የወንጀል ታሪክ በወንጀል ህጋችን በሶስት የተለያየ ደረጃ ወይም አኳኋን ቅጣትን ለማክበድ የሚያገለግል እንደሆነ በልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ተመልክቶ እናገኛለን።
- የመጀመሪያውና በመርህ ደረጃ በቀደመ የወንጀል ታሪክ ቅጣት የሚከብድበት ሁኔታ በወንጀል ህጉ ቁጥር 84 (1) ሐ በተመለከተው አግባብ በጠቅላላ ማክበጃነት ሲሆን ይህንንም በጠቅላላ ማክበጃ የቅጣት አሰላል ለመመልከት እንደሞከርነው በልዩ ክፍሉ ድንጋጌ ስር ለተመለከተው ቅጣት ጣራ ድረስ ብቻ ለማክበድ የሚቻልበት ሁኔታ ነው።

የቀጠለ

- ከዚህ በተለየ የቀደመ የወንጀል ታሪክ ቅጣት የሚያከብድበት ሁለተኛው ሁኔታበልዩ ድንጋጌው ስር የቀደመ የወንጀል ታሪክ ካለው ቅጣቱ በዚህ ደረጃ ይከብዳል ብሎ በሚደነግግበት ጊዜ ነው።
- በመሆኑም በዚህ አግባብ ራሱ ድንጋጌው የወንጀል ሪከርድን ምክኒያት በማድረግ ያከበደ እንደሆነ ሪከርድ በአንቀጽ 84 (1) ሐ መሰረት በጠቅላላ ማክበጃነት ሳይሆን በራሱ ድንጋጌው ባከበደው ልክ ቅጣቱ የሚከብድ ይሆናል።
- ለምሳሌ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 525 (2) ሰ እንዲሁም 539 (2) ድንጋጌዎችን ብንመለከት በራሳቸው ቅጣትን አክብደዋል። በመሆኑም እነዚሁ ድንጋጌዎች በሚያስቀምጡት መሰረት ቅጣቱ ይከብዳል።

የቀጠለ

- ሶስተኛው ሁኔታ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 67 ላይ የተደነገገው የደጋጋሚነት ወንጀል ነው።ይህ የቅጣት ማክበጃ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ነው።
- በድንጋጌው ላይ እንደተመለከተው “ወንጀል አድራጊው በደጋጋሚነት ወንጀል አድርጓል ብሎ ፍርድ ቤት ቅጣት የሚያከብደው የተወሰነበትን የእሥራት ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመበት ወይም ይህ ቅጣት በይቅርታ ከቀረለት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ መነሻ ቅጣቱ ስድስት ወር የሆነ ቀላል እስራት ማስቀጣት የሚችል አዲስ ወንጀል አስቦ ያደረገ እንደሆነ ነው።”
- በዚህ ድንጋጌ መሰረት የአንድ ወንጀል አድራጊ የቀደመ የወንጀል ታሪኩ ደጋጋሚ ወንጀለኛ በማስባል ቅጣት የሚከብደው 5 ቅድመሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው።

የቀጠለ

- የመጀመሪያው ቅድመሁኔታ በቀደመው ጥፋተኝነቱ የተፈረደበት የእስራት ቅጣት መሆኑ የሚለው ሲሆን ከዚህ በተለየ ቀደም ሲል የተቀጣው በመቀጮ ወይም በግዴታ ስራ ከሆነ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል ምንም ቢሆን በደጋጋሚነት ቅጣቱ የሚከብድበት አይሆንም።
- እዚህ ላይ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው በልዩ ሁኔታ ተከሳሹ ጥፋተኛ ተብሎ ነገር ግን የቅጣት ውሳኔ ሳይተላለፍበት የጥፋተኝነት ውሳኔው የሚገደብለት ቢሆን አንቀጽ (191) ገደቡ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ አስቦ አዲስ ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ በወንጀል ህጉ ቁጥር 200 (3) መሰረት የደጋጋሚነት ቅጣት ማክበጃ ይፈጸምበታል። ስለሆነም በዚህ ልዩ ሁኔታ ብቻ የእስራት ቅጣት ሳይወሰንበት የደጋጋሚነት መርህ ተፈጻሚ የሚሆንበት አግባብ ነው።

የቀጠለ

- ሁለተኛው ቅድመሁኔታ ይህንኑ የእስራት ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈጸመ በኋላ ወይም ይህ ቅጣት በይቀርታ ከቀረለት በኋላ በአምስት አመት ውስጥ ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ የሚለው ነው።
- በመሆኑም ከአምስት አመት በኋላ ምንም አይነት ወንጀል ቢፈጽም በደጋጋሚነት ሳይሆን በመደበኛ የቅጣት ማክበጃ አንቀጽ (84(መሰረት ቅጣቱ የሚከብድ ይሆናል።

የቀጠለ

- ሶስተኛው ቅድመሁኔታ አሁን የተከሰሰበት ወንጀል መነሻ ቅጣቱ 6 ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ መሆኑ የሚለው ነው።
- እዚህ ላይ አከራካሪው ነገር “መነሻ ቅጣቱ 6 ወር ቀላል እስራት” የሚለው ፍ/ቤቱ የጥፋተኝነት ውሳኔ ካስተላለፈ በኋላ የሚይዘውን መነሻ ቅጣት ነው ወይስ ህግ አውጪው በህጉ ልዩ ድንጋጌ ላይ ያስቀመጠውን መነሻ የሚመለከት ነው የሚለው ነው።
- የወንጀል ህጉን ሀተታ ዘምክኒያት በምንመለከትበትጊዜ ፍ/ቤቱ የሚይዘውን መነሻ ቅጣት የሚመለከት እንደሆነ አስቀምጧል።

የቀጠለ

- ይሁንና እንዲህ አይነቱ የወንጀል ጉዳይ በግልጽ በህግ አውጪው መቀመጥ ያለበት በመሆኑ እንዲሁም አቃቢ ህግ ይህን አይነቱን የቅጣት ማክበጃ ለመስጠት የሚችለው በወንጀለኛ ሥነሥርአት ህጉ ቁጥር 149 (3) መሰረት ከጥፋተኝነቱ ውሳኔ በኋላ እንጂ ፍ/ቤቱ የመነሻ ቅጣት ከያዘ በኋላ ባለመሆኑ በአፈጻጸም ጊዜ ለአሰራር ችግር ይፈጥራል። በመሆኑም አሳማኝ የሚሆነው ህግ አውጪው ያስቀመጠው የልዩ ድንጋጌው መነሻ የሚለው ነው።
- አራተኛው ቅድመሁኔታ አዲስ ወንጀል ማድረግ የሚለው ነው።
- የመጨረሻውና አምስተኛው ቅድመሁኔታ ወንጀሉ የተፈጸመው ታስቦ የሚለው ነው። በቸልተኝነት ከሆነ ደጋጋሚ የሚባል አይሆንም።

የቀጠለ

- ከነዚህ አምስት ቅድመሁኔታዎች መካከል አንዱ እንኳ ያልተሟላ ከሆነ የቀደመው የወንጀል አድራጊው ሪከርድ በመደበኛው ማክበጃነት አንቀጽ 84 (1) ሐ መሰረት ቅጣት የሚያከብድ እንጂ በደጋጋሚነት ቅጣት የሚያከብድ አይሆንም።
- ወንጀለኛው ደጋጋሚ መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ በወንጀል ህጉ ቁጥር 192 መሰረት የሚደረግ ገደብ ተጠቃሚ የሚሆን እንዳልሆነ የዚሁ ህግ ቁጥር 194 ይደነግጋል።

የቀጠለ

- በደጋጋሚነት ቅጣት የሚከብድበትን ሁኔታ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 188 ደንግጓል። በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት በአንቀጽ 67 አግባብ ወንጀለኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከሆነ ፍ/ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት በማለፍ መወሰን ይችላል።
- እንደነገሩ ሁኔታ ፍ/ቤቱ በሕጉ ልዩ ክፍል ለአዲሱ ወንጀል ወይም ከአዲሶቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ከባድ ለሆነው ወንጀል የተደነገገውን ጣራ ቅጣት እጥፍ እስኪሆን ቅጣቱን ሊያከብድ ይችላል።

የቀጠለ

- የዚህ ንዑስ ቁጥር አቀራረጽ በደጋጋሚ ወንጀል ጊዜ ፍ/ቤቱ ወንጀለኛው ምን ያህል ይቀጣ የሚለውን ለመወሰን ፍ/ቤቱ ስልጣን ‘discretionary power’ የተሰጠው መሆኑን የሚያሳይ ነው።
- በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (2) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ እንደተደነገገው በተደጋገሙት የወንጀሎች ዓይነትና ብዛት እንዲሁም በወንጀለኛው ጥፋተኛነትና በድርጊቱ አደገኛነት መጠን ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ከፍተኛ ቅጣት ሳይከተል ለቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ሊያሳድግ ይችላል

የቀጠለ

- ነገር ግን በዚሁ ንዑስ ቁጥር ፓራግራፍ ሁለት ላይ እንደተመለከተው ወንጀለኛው ልማደኛ ደጋጋሚ ከሆነ ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት እጥፍ በማለፍ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ማሳደግ አለበት።
- ልማዳዊ ደጋጋሚ የሚለው አንድን የወንጀል ተግባር በተደጋጋሚ መፈጸም እንደሆነ በሀተታ ዘምክኒያቱ ላይ ተመልክቷል።
- በዚህ ድንጋጌ መሰረት ቅጣት ሲከብድ ለጠቅላላው የወንጀል አይነት ከተቀመጠው ከፍተኛ ቅጣት አንቀጽ (106/108) አሳልፎ መቅጣት የሚቻል አይሆንም።

ሐ የቅታት ማክበጃና ማቅለያ ተቀላቅለው ሲገኙ ቅጣት የሚወሰንበት አግባብ

- የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክኒያቶች ብዙ ጊዜ ተቀላቅለው ይገኛሉ። በዚህ ጊዜ ቅጣቱ በምን መልኩ ይወሰናል የሚለውን የወንጀል ህጉ ቁጥር 189 ደንግጎ ይገኛል።
- በዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት በአንድ ወንጀል ላይ ቅጣት የሚያከብዱና የሚያቀሉ ጠቅላላ ምክንያቶች በተደራረቡ ጊዜ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማክበጃ ምክንያቶችን ከግምት በማስገባት ቅጣቱን ያከብድና /አንቀጽ 183/፣ ቀጥሎ የሚያቃልሉትን ምክንያቶች መሠረት አድርጎ ቅጣቱን ይቀንሳል /አንቀጽ 179፣ 180። ይህም የተከሳሹን መብት ከመጠበቅ አንጻር የሚታይ ነው።

የቀጠለ

- በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (2) ላይ እንደተመለከተው ሁለቱ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክኒያት የሆኑት ተደራራቢ ወንጀሎችና ደጋጋሚነት ተቀላቅለው በሚገኙበት ጊዜ በመጀመሪያ ለተደራራቢ ወንጀሎቹ ቅጣት ይወሰንና በደጋጋሚነቱ ቅጣቱ የሚከብድ ይሆናል።
- እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክኒያቶችና ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክኒያቶች ተደራርበው ሲገኙ ቅጣቱ በምን መልኩ ይወሰናል የሚለው ነው፣
- የወንጀል ህጉ ይህንን በተመለከተ በግልጽ የደነገገው ነገር ባይኖርም በመጀመሪያ ሊወሰን የሚገባው በልዩ ማክበጃው ቅጣት ከከበደ በኋላ የጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክኒያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣት የሚከብድ ይሆናል። ምክኒያቱም አንድ የጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክኒያት ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባለ ከሆነ ለሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ተግባራዊ መሆን ስላለበት፤ እንዲሁም ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከሆነም በደጋጋሚነቱ ቅጣቱ ከከበደ በኋላ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃውን ተጠቅሞ ቅጣቱን ማክበድ ስለሚኖርብን ነው።

3የመቀጨ ቅጣት አፈጻጸም

- የመቀጨ ቅጣት ፍ/ቤቱ በተለያዩ ምክኒያቶች ሊወስን የሚችል ይሆናል። ከነዚህም መካከል የልዩ ድንጋጌው መቀጨን እንደቅጣት ያስቀመጠ እንደሆነ፣ ወይም በልዩ ሁኔታ በመቀጨና በእስራት ወይም በአማራጭ ቅጣት እንዲቀጣ ልዩ ድንጋጌው የሚያስቀምጥ ከሆነ፤ ወይም ፍ/ቤቱ የስራት ቅጣትን ወደመቀጨ እንዲለውጥ በሚፈቅዱ ሁኔታዎች ላይ የመቀጨ ቅጣት ሊወስን ይችላል።
- በወንጀል ህጉ ቁጥር 90 (1) መሰረት በወንጀል ምክኒያት የሚጣሉ መቀጨዎች ገቢነታቸው ለመንግስት ሲሆን መከፈል ያለባቸውም በገንዘብ ነው።
- ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር መቀጨው ለተፈጥሮ ሰው ከብር አሥር እስከ ብር አስር ሺህ እንዲሁም ህጋዊ ሰውነት ላለው ድርጅት ከአንድ መቶ ብር እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ ይሆናል።

የቀጠለ

- ይህ ጠቅላላ የቅጣቱ መጠን በቁጥር 92 ላይ በተመለከተው የቅጣት ማክበጃ ምክኒያት ከፍ ተደርጎ ሊወሰን ይችላል።
- ይሄውም ወንጀለኛው ወንጀል ያደረገው የአፍቅሮ ንዋይ ስሜት አነሳስቶት ወይም ወንጀለኛነትን እንደሙያ ሥራ በመቁጠር በዚሁ ሥራው ጥቅም ሊያገኝ የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ባጋጠመው ቁጥር በእንደዚህ ያለ ተግባሩ መጠቀምንና ይህንኑ እንደጥቅም ማግኛ የመደበው ሆኖ የኑሮውም ሁኔታና በወንጀሉ ያገኘው ጥቅም ይህንኑ ተግባሩን በግልጽ የሚያሳይ በቂ ምክንያት መሆኑ የተገመተ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ቅጣቱን በማሳደግ እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ የሚደርስ መቀጮ ሊወስንበት ይችላል።

የቀጠለ

- የአፍቅሮ ንዋይ መነሾ የተደረገውን ወንጀል የማያቋቁም ቢሆንም ስለእንደዚህ ያለው ጥፋት የሚገባውን ቅጣት በሚወስኑት በሕጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች ላይ መቀጮ ተገልጾ ያልተመለከተ ቢሆንም እንኳ ፍርድ ቤቱ ከሚወስነው የእሥራት ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ጋር መቀጮንም አጣምሮ ሊፈርድ ይችላል።
- ምንጊዜም ቢሆን መቀጮው በወንጀሉ ድርጊት ምክንያት የተገኘውን ጥቅም ከመውረስ በተጨማሪ የሚወሰን ይሆናል።

የቀጠለ

- የመቀጮ መጠኑን ፍ/ቤቱ ሲወሰን በህጉ ቁጥር 90 (2) ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማለትም የወንጀሉን ክብደት፣ የአደገኛነቱን መጠን የሀብቱን ሁኔታ፣ የገቢ ምንጩን፣ ስለቤተሰቦቹ አስተዳደር ያለበትን ሸክም፣ የሙያ ሥራውንና ከሥራው የሚያገኘውን ገቢ መጠን፣ ዕድሜውንና የጤንነቱን ሁኔታ በማመዛዘን ነው።
- እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በወንጀል ህጉ ቁጥር 82፣ 84 እንዲሁም 86 መሰረት የሚያዙ የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክኒያቶች ለገንዘብ መቀጮ ያገለግላሉ? የሚለው ነው።

የቀጠለ

- ይህንን በተመለከተ በሁለት መልኩ ክርክሮች ይነሳሉ። የመጀመሪያው ክርክር የወንጀል ህጉ ቁጥር 82፣ 84 እና 86 ለእስራት ቅጣት በሚል ብቻ የተደነገጉ ባለመሆናቸው በነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የሚገኙ የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክኒያቶች ለገንዘብ መቀጮም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል የሚል ነው።
- በሌላ በኩል የሚነሳው ክርክር ፍ/ቤቱ መቀጮን በቅጣትነት ሲወስን የመቀጮውን መጠን የሚወስንበት አግባብ በህጉ ቁጥር 90 (2) እና 92 ላይ የተመለከተ በመሆኑ ከላይ የተመለከትናቸው ድንጋጌዎች የመቀጮ ቅጣትን በማቅለልም ሆነ በማክበድ ረገድ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

የቀጠለ

- ከነዚህ ሁለት ክርክሮች አንጻር የፊደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በግልጽ በጭብጥነት ይዞ በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ባይሰጥም በውሳኔ አሰራር እረገድ በአንቀጽ 82፣ 84 እና 86 መሰረት የሚያዙ መደበኛ የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክኒያቶችን በአንድአንድ ውሳኔዎቹ ላይ ለምሳሌ በቅጽ 16 መዝገብ ቁጥር 96954 መደበኛ የቅጣት ማቅለያ ምክኒያትን ለገንዘብ መቀጮ የተገለገለበትን ሁኔታ እንዲሁም በተመሳሳይ ቅጽ መዝገብ ቁጥር **96078** መደበኛ የቅጣት ማቅለያ ምክኒያቶችን ለእስራት ቅጣቱ ከተጠቀመ በኋላ ለገንዘብ መቀጮው ሳይጠቀምበት ቀርቷል።
- በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ላይ ሰበሩ ወጥነት ባለው መልኩ ውሳኔዎችን እየሰጠነው ለማለት አይቻልም።

የቀጠለ

- በወንጀል ህጉ ቁጥር 91 ላይ እንደተደነገገው የህጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌ መቀጮንና እሥራትን በአማራጭ የደነገገ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የወንጀሉን ክብደትና የወንጀለኛውን ሁኔታ በማመዛዘን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ሁለቱንም አጣምሮ ሊወስን ይችላል።
- በመሆኑም በአማራጭ በእስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣ በሚል የተደነገገ ስለሆነ የግድ እንዱን ብቻ ነው ሊቀጣ የሚገባው ሊባል አይገባም።
- የመቀጮ ቅጣት አከፋፈልን በተመለከተ በወንጀል ህጉ ቁጥር 93 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቷል
- የመቀጮ ቅጣት መከፈል ያለበት በመርህ ደረጃ ወዲያውኑ ነው።

የቀጠለ

- ነገር ገን ተቀጪው የተቀጣውን መቀጮ ወዲያውኑ መክፈል ያልቻለ እንደሆነ እስከስድስት ወር ጊዜ ተሰጥቶት እንዲከፍል ወይም ፍ/ቤቱ ካመነበት ጥቂት በጥቂት እንዲከፍል እስከ3 አመት የመክፈያ ጊዜ ይሰጠዋ።
- ለነዚህም ክፍያዎች በአግባቡ መከፈል ፍ/ቤቱ ተቀጪው ተገቢነው የሚለውን የሰው ወይም ግዙፍ መያዣ እንዲያሲዝ ያደርጋል።
- ከነዚህ በአንዱ አግባብ መቀጮው ያልተከፈለ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተቀጪው ለመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ስራ በመስራት ቅጣቱን እንዲፈጽም በማድረግ ወይም ይህ ካልሆነ የግድ የግዴታ ስራ እንዲሰራ በማድረግ የተቀጣውን መቀጮ እንዲከፍል ማድረግ ይኖርበታል።